# የዐማራ ትግል የጋራ ምክር ቤት መግለጫ

በኢትዮጵያ የረዥም ዘመን ታሪክ ውስጥ የውጭ ኃይሎች አገራዊ ሉዐላዊነቷን ለማፍረስና ውስጣዊ አንድነቷን ለማዳከም የተለያዩ ሴራዎችን ተጠቅመዋል። የውጭ ኃይሎች በቀጥታ ወረራና በተለያዩ ጫናዎች ያልተሳካላቸውን አገር በቀል ባንዳዎችን በመመልመል፣ በማሰልጠንና በማሰማራት ብዙ ሰርተዋል። በዚህም ሳቢያ የዐማራን ልዕልናና አገር ወዳድነቱን የሚጠሉ በድንቅ ብሂሉና ታሪኩ የሚቀኑ፣ በፈጠራ የሀሰት ትርክት የተጠመቁ፣ የበታችነት የሚሰማቸው ፀረ-ዐማራ የጎሳ ልሂቃን ቀስ በቀስ ወደ ሥልጣን መምጣት ችለዋል። የግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሤ ንጉሠ ነገሠት ዘኢትዮጵያን መንግስት ባስወገደው ፋሽስታዊው ደርግና በግራ ፖለቲካ አቀንቃኞች እያቆጠቆጠ የመጣው ፀረ-ዐማራ ትርክት የዐማራን ሕዝብ ለማጥፋት ህገ መንግስት ቀርጾ ስልጣን ላይ በወጣው ትህነግ በይፋ በኢትዮጵያ ላይ እንዲናኝ ተደረገ። አሁን ደግሞ በኢትዮጵያ አገረ መንግስት ምስረታ ላይ ይህ ነው የሚባል አሻራ የሌለው የትህነግን ዐማራ-ጠል መመሪያንና የሰነበተ ጥላቻውን ሙሉ በሙሉ ዐማራን በማጥፋት እወጣዋለሁ ብሎ በተነሳ ወራሪ ኦሮሙማ ተተካ። ሲፈራረቅ የቆየውን ዐማራ-ጠል ስርዓትና አስተሳሰብ ለመቀልበስ ጥረት ሲደረግ ቆይቷል። በተለይ ትህነግ ሥልጣን እንደተቆጣጠረ ከኦነግ ጋር በመቀናጀት በግልጽ መንግስታዊ የዐማራ የዘር ማጥፋት ሲካሄድ፣ የዐማራን ህልውና የመታደግ ትግል በፕሮፌሰር አስራት ወልደዬስ ተጀምሮ፣ በጀነራል አሳምነው ፅጌ የጎመራው የህልውና ትግል በቅርቡ በአማራ ፋኖ ተቀጣጥሎ ወደ ሕዝባዊ የፋኖ ትግል ባጭር ጊዜ ተሸጋግሮ ለዐማራውና ለአገሩ ትልቅ ተስፋ ሆኗል። የኢትዮጵያ ሕዝብም ፋኖ አዲስ አበባ ገብቶ በዐማራ ጥላቻ ላይ የተመረኮዘውን አስተሳሰብና አሰራር ተወግዶ ኢትዮጵያ እፎይታ እንድታገኝ በጉጉት እየጠበቀ ነው።

ይህ ከሃምሳ አመታት በላይ በተከፈለ መስዋዕትነት ምክንያት የተቀጣጠለው መራር የህልውና ትግል ሲደመደም፣ ከዚህ በፊቱ በዐማራ መስዋዕትነት የሚገኘው ድል ራሱንና ኢትዮጵያን በሚያጠፉ መሰሪዎች እንዳይተካ ትልቅ ጥንቃቄ ያስፈልጋል። የኢትዮጵያን ዕሴት ታሪክ ባህልና ትውፊት የተላበሰ ኢትዮጵያዊ አስተዳደር መመለስ አለበት። በዚህም መሰረት በየቦታው የዐማራን ትግል አቅጣጫ ሊወስኑ በሚችሉ መንገዶች ሁሉ የሚታገል ዐማራ ሊመክር ይገባል። ምክክሩ በተግቢው መንገድ እንዲጓዝ የዐማራ ትግል የጋራ ምክር ቤትን ማዋቀር አስፈልጓል።

የዐማራ ትግል የጋራ ምክር ቤት ዕውነተኛ የዐማራ ህልውና ትግልን ተቀብለው በሚያደርጉት እንቅስቃሴ አላስፈላጊ የርስ በርስ ፉክክርና መጠላለፍ ውስጥ ሳይገቡ፣ ይልቁንም ተመካክረው እንዲሰሩ የዐማራ ድርጅቶችንና ግለሰቦችን አካቶ የትግል ምሰሶው እንዲጠናከር ወቅቱ የሚጠይቀው መሰባሰቢያ ጎጆ ነው። የዐማራ ትግል የጋራ ምክር ቤት የዐማራ ፖለቲካ ድርጅቶችን፣ የዐማራ ሲቪክ ማህበራትን፣ የዐማራ ሚዲያዎችን፣ የዐማራ ግለሰብ አንቂዎችን፣ የዐማራ ዘርፈ ብዙ ባለሞያዎችን፣ የዐማራ የሃይማኖት መሪዎችን፣ እንዲሁም በጾታ በዕድሜና በመሳሰለው በምናውቀውና ገና ባላወቅናቸው የዐማራ ድርጅቶች ሁሉ ተሰባስበው በጋራ የሚመክሩበት ተቋም ነው።

## ዓላማው

በዐማራ ጉዳይ ያገባናል የሚሉ ዕውነተኛ የዐማራ ድርጅቶች ስለ ዐማራው የአሁኑንና የወደፊት ዕጣ ፋንታ የሚመክሩበት፣ ዕውነተኛውን ከሰርጎ ገብ ነጥሎ ለማወቅ የሚችሉበትና የአካሄድ ልዩነቶቻቸውን አጥብበው ተስማምተው ወይም ተዋህደው የሚጠነክሩበትን የትግል አካሄድ የሚያመቻች ተጠሪነቱ ለዐማራው የሆነ የትግል የጋራ ምክር ቤት ነው።

### የዐማራ ትግል የጋራ ምክር ቤት

1. መሬት ላይ ያለውን የፋኖ ታሪካዊ ገድል ተንተርሶ በየቦታው በዐማራ ስም የሚፈጠሩ ድርጅቶች መብዛትና እርስ በርስ የመሻኮት ችግር ለውስጥና ለውጭ ጠላቶች ተጋላጭ እንዳይሆኑ፣ ለጠላቶች በር እንዳይከፍቱ፣ ሁሉም ድርጅቶች ተሰባስበው ተናበውና ተማክረው በጋራ እንዲሰሩ ማመቻቸት ነው።
2. በመረጃና በማስረጃ ያልተደገፉ ከግለሰብና ከቡድን እንዲሁም ከግል አንቂዎች የሚነገሩና የሚፃፉ የዐማራውን አንድነት የሚፈታተኑ ነገሮች እንዲታረሙ፣ የፋኖ ወንድሞችና እህቶች በተሳሳተ መረጃ አደጋ ላይ እንዳይወድቁ፣ ባጠቃላይ ለጠላት በር እንዳይከፍትና ዐማራው ለተራዘመ ትግል እንዳይዳረግ በትጋት ይሰራል።
3. የዐማራ-ጠል ቡድኖችና ግለሰቦች የሚያራምዱትን ተከትሎ ዐማራው መሪ የለውም፣ ወጣቱና ሽማግሌው አይግባባም፣ የተማረና ያልተማረው አይተዋወቁም፣ ወዘተ አባባሎች እንዲስተካከሉና ሁሉም በጸና መንፈስ ለትግሉ እንዲሰለፍ ጥረት ማድረግ ነው።
4. የዐማራ ድርጅቶች ሳይጠላለፉ በአንድ የጋራ ግብ ላይ መታገል እንዲችሉ ሁሉንም የዐማራ ታጋዮች፣ ምሁራን፣ የግልና የቡድን ሚዲያዎችን በማሳተፍ መርሆዎችን መስፈርቶችንና ተጠያቂነትን ማእከል ያደረገ አሰራር እንዲጎለብት የሚሰራ ምክር ቤት ነው።

## ወቅታዊ ተግዳሮት

### በዐማራ ድርጅቶች መካከል ተናቦና ተስማምቶ ያለመስራት ዘርፈ ብዙ አደጋዎችን ሊያስከትል ይችላል።

1. በተናጥል ያለው ሩጫ ለብአዴን የኦሮሙማ ተላላኪዎች በር ይከፍታል፤ ለኦሮሙማ ኦነግና ለትህነግ ሰርጎ ገቦች ያጋልጣል።
2. መሬት ላይ ያሉ ታጋዮችን በግላዊና ቡድናዊ ጥቅምና ስልጣን እርስ በርስ እንዲከፋፈሉ በማድረግ ለጠላቶች በር ይከፍታል።
3. የዐማራ ስነ ልቦና በሌላቸውና ዐማራ ሲታረድና ሲፈናቀል ለምን ብለው ባልጠየቁ፣ ቆመው ሲያጨበጭቡ በነበሩ ግለሰቦችና ቡድኖች የዐማራ ትግል እንዲጠለፍ ምክንያት ይሆናል።

4. የኦነግ ኦሮሙማን አገዛዝ በመፃረር የሚታገል ሀይል ሁሉ ስትራቴጂካዊ ወዳጅ ቢሆንም፣ የዐማራን ትግል በኢትዮጵያዊነት መጥለፍ ግን በኢትዮጵያዊነት ስም ለትህነግ አሁን ደግሞ ለኦሮሙማ የሀር ምንጣፍ አንጥፈው እንደከሰሙት ዐማራ ላይ አደጋ ሊያስከትል ይችላል።
5. አማራ ጠሎችና አጋሮቻቸው በሚሰጡን አጀንዳና በሚያጠምዱልን መሰናክሎች ምክንያት ጠላትና ወዳጅን አንጥሮ በማውቅ፣ ለአማራውና ለኢትዮጵያ ዘላቂ መፍትሄ የሚያመጡ ስልትና ግቦችን በመቅረፅ፣ የአማራውን የህልውና ትግል ድላችንን ሊያዘገየው ይችላል።
6. የዐማራ ጠሎችን ሴራዎች በበቂ አለመገንዘብ፣ አማራው ወገናዊ መናበብ እንዳይፈጥር፣ ታማኝ መሪዎች እንዳያወጣ፣ ጠንካራ ተቋሞች እንዳይገነባ ያደርጋል።
7. በአገር ቤት በሽምግልና ስም፣ በውጭ ኃይሎች እናደራድራችሁ (እናነጋግራችሁ) ስም የሚፈጠር ችግሩን ያልተረዳ ግንኙነት የህልውናውን ትግል ዘላቂ መፍትሄ በማምጣት እንዳይደመደም ያደርጋል፤

የአማራ ድርጅቶችና አስተባባሪዎች በተናጥል እየሰሩ ስለሆነ የትኛው ከየትኛው መሬት ካለ አካል ጋር እንደሚሰራ ካልታወቀ አሁንም ለጠላቶች መንገድ መምራት ይሆናል። ስለዚህ ይህ አደጋ ትግሉን ሊጎዳ እንደሚችል ተረድቶ፣ ተናበና ተቀናጅቶ መስራት ምርጫ ሳይሆን ግዴታ ነው።

## የዐማራ ትግል የጋራ ምክር ቤት በምን ይለያል?

አብዛኛዎቹ የዐማራ ድርጅቶችና ሚዲያዎች የተቋቋሙት በዐማራ ሕዝብ ላይ ያነጣጠረ ግፍና መከራን ለመታደግ ያስኬዳል ብለው ባመኑበትና በተረዱት ልክ መሬት ላይ ያለውን ትግል ለማገዝ ነው። የዐማራ ትግል የጋራ ምክር ቤት የዓለም አቀፍ ተሞክሮን በመረዳት፣ በተለያዩ ሀገራት ላይ የደረሰውን የሀገር መፍረስ አደጋ በሀገራችን ኢትዮጵያ እንዳይደገም ለመከላከል፤ በቅድሚያ ዐማራን አንድ አድርጎ እየተናበበ የህልውና ትግሉን እንዲያሸንፍ የሚያስፈልገውን ማንኛውንም ግብአት ማቅረብ ነው። በዚህ የህልውና ትግል ሂደትም ዋናው ትኩረታችን እንዳለ ሆኖ ከሌሎች ማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ሀገራዊ አንድነትን የሚያመጣ ምክክር ማድረግ ነው።

የዐማራ ትግል የጋራ ምክር ቤት ማንኛውም የዐማራ ድርጅት፣ ቡድን፣ የማህበረሰብ አንቂ ግለሰብ፣ ወዘተ የዐማራውን ትግልና አንድነቱን እስካልጎዳ ድረስ የአሰራር ልዩነቶችን አክብሮ ተስማምቶና ሰርቶ የሚያሰራ ተቋም ነው። የዐማራ ትግል የጋራ ምክር ቤት ተሰባስበው የተገኙትን ዐማሮች በሙሉ በስራ ዘርፍ ከፋፍሎ ሁሉንም ድርጅቶችና ግለሰቦች በሚያሳትፍ መልኩ ለዐማራው የሚበጀውን መከወን ነው። የዐማራ ትግል የጋራ ምክር ቤት ራሱን ለማሻሻል በማያቋርጥ የለውጥ ሂደት ላይ ተመርኩዞ በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚና ማኅበራዊ ጉዳዮች ሁሉ ተግቶ በማትጋት ለመቃዝ ቆርጦ የተነሳ ተቋም ነው። ትግሉን ለማሳለጥ የሚረዱ መምሪያዎችን

አቋቁሟል። እነዚህም፤ የህልውና ትግል፣ ዲፕሎማሲ፣ ጥናትና ምርምር፣ የድርጅት ጉዳይ፣ የፖለቲካ ጉዳይ፣ የሰው ኃይልና አቅም ግምባታ፣ የሀብት ማሰባሰብ፣ የመረጃና ትንታኔ፣ ቴክኖሎጂና ኮሚኒኬሽን ናቸው። በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ መሬት ላይ ባለው ትግል ከሚንቀሳቀሱ አርበኞቻችን ጋር ዐማራ ጠሉን አስተዳደር አስወግዶ እኩልነት ፍትሃዊነትና ዴሞክራሲ እንዲሰፍን የሚታገል ምክር ቤት ነው።

## ወገናዊ ጥሪ

ከላይ ዓላማውና ምግባሩ በዝርዝር በተገለጸው የዐማራ ትግል የጋራ ምክር ቤት ውስጥ ተሳትፎ ለማድረግና ለወገኑ በአቅሙና በችሎታው ግዴታውን ለመወጣት የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት።

1. በትህነግ ኢሐዴግ/በኦነግ ኦሮሙማ የአፓርታይድ አገዛዝ ፖሊሲና አፈጻጸም ላይ ተመስርቶ ዐማራው በማንነቱ ተለይቶ የዘር ማጥፋትና የዘር ማጽዳትን ጨምሮ ለተፈጸሙበት አሰቃቂ ወንጀሎች ሙሉ ዕውቅና የሚሰጥ፣ አስፈላጊው ፍትህ እንዲገኝም በቁርጠኝነት የሚታገል፤
2. በውጭ ሃይሎችና አገር በቀል የዐማራ ጠላቶች የሚያቀነቅኑትን የሃሰት ትርክት አጥብቆ የሚቃወምና ትርክቱን ለመናድ በጽኑ የሚታገል፤
3. የዐማራ ሕዝብ በተደራጁ ፀረ ዐማራ ቡድኖችና ግለሰቦች በተለየና በተጠና መንገድ የሕልውና አደጋ የተደቀነበት መሆኑን የሚያምን፤
4. ዐማራው ያለበትን የህልውና አደጋ ለመቀልበስ በሚደረገው ትግል በቁርጠኝነትና በግምባር ቀደምትነት ለመሰለፍ የተዘጋጀ፤
5. ከብልጽግና/ኦሮሙማው መራሹ አገዛዝ ጋር በድርድር ስልጣን ተጋርቶ ጥገናዊ ለውጥ ማምጣትን የማይቀበል፣ የዐማራ የህልውና ትግል ስር ነቀል ለውጥ በማምጣት መደምደም እንዳለበት የሚያምን፤
6. በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ከብአዴን፣ ከኦሕዴድ፣ ኦነግ፣ ብልጽግናና መሰል ድርጅቶችና አጋሮቻቸው ጋር የፖለቲካም ሆነ የሌሎች ጥቅም ግንኙነት የሌለው፣ ያልነበረው፤
7. የደርግ፣ የወያኔ ወይም የኦሮሙማ ስርዓት ሲፈጽም በነበረው ወንጀል በቀጥታም ሆነ በአማካሪነት ያልተሳተፈ።

**ትስስራችን በዓለማ አንድነታችን!**

የዐማራ ትግል የጋራ ምክር ቤት
ታኅሣስ ፰ ቀን <u>፳፻፲፮</u> ዓ.ም

ዐማራ በጀግኖች ልጆቹ ክንድ ህልውናውን ያስከብራል!!!
ድል ለአማራ ህዝብ !